የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
Ethiopian Capital Market Authority

ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም

## ጋዜጣዊ መግለጫ

**በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ መስጠት የሚያስችል መመሪያ በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ወደ ትግበራ እንዲገባ ተደረገ፡፡**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 1248/2013 መሰረት የተቋቋመ የፌደራል መንግስት ተቋም ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 108 መሰረት መመሪያ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል። በዚህ መሠረት ባለሥልጣኑ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ ለተዛማጅ ውሎች እና ለያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች ፈቃድ የሚሰጥበትና የሚቆጣጠርበትን "የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር መመሪያ" አዘጋጅቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር አስመዝግቧል።

በመሆኑም "የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1009/2016 ከሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል።

መመሪያው በባለሥልጣኑ እንዲዘጋጅ እና እንዲወጣ በካፒታል ገበያ አዋጅ ከተመለከቱት ውስጥ አንዱ ሲሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማለከ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች፣ ገበያው አባላቱን እንዴት እንደሚቆጣጠር፣ ገበያው አባለቱን መቆጣጠር የሚያስችለው የውስጥ ደንብ በባለሥልጣኑ አጸድቆ ማውጣት እንደሚገባው፣ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት እንዴት እንደሚያቀርብ እና በአጠቃላይ አሰራሩ ምን መምሰል እንዳለበት የተለያዩ ደረጃዎችን ያስቀምጣል።

ይህ መመሪያ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያን ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ሲሆን የመንግስት እና የግል ድርጅቶች ገበያውን በመጠቀም የድርጅቶችን የድርሻ እና የብድር ሰነዶችን በመሸጥ እና ገንዘብ በመሰብሰብ ፕሮጀክቶችን ለመስራት አቅም ለመፍጠር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሌላ በኩል መመሪያው መውጣቱ የድርሻ ወይም የብድር ሰነድ መግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ወይም ኢንቨስተር ፈቃድ ካለው ገበያ አስፈላጊው ቁጥጥርና ግልጸኝነት በተሟላበት የግብይት አሰራር፣ ፈቃድ ባለው ተገበያይ አማካኝነት የተፈቀዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት እና ለመሸጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል።

ይህ እርምጃ በሀገራችን በተበታተነ መልኩ የሚደረገውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ወደ አንድ ፈቃድ ወደሚሰጠው እና ቁጥጥር ወደሚደረግበት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በማምጣት ዘርፉ ለተዋናዮቹ እና ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ የጎላ ይሆናል።

መመሪያው በመቋቋም ላይ ለሚገኘው የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አ.ማ በመመሪያው መሠረት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ ፈቃድ በመስጠት ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል ነው።

መመሪያውን ለማግኘት የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ድረ-ገጽ (ecma.gov.et) ይጎብኙ።

### ስለ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ለማሳደግ እና ቁጥጥር እንዲያደርግ የተቋቋመ ሲሆን በካፒታል ገበያ አዋጁ አንቀፅ 3(1) መሰረት ባለስልጣኑ ህጋዊ ሰውነት ያለው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆነ ተቆጣጣሪ ተቋም ነው። ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢንቨስተሮች የመጠበቅ፣ የገበያውን ተዐማኒነት የማረጋገጥ ፣ ስርዐታዊ ስጋቶችን የመቀነስ እና ገበያውን የማሳደግ አላማን በማንገብ በጠንካራ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና ስልታዊ ስትራተጂዎች እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው።

### ለጥያቄዎች እና ለተጨማሪ መረጃ

ሳሮን ወ/ገብርኤል
የኮምኒኬሽን ሃላፊ
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
ስልክ- 011-5-57-81-62
ኢሜል- communications@ecma.gov.et
ለበለጠ መረጃ ድረገጻችንን ይጎብኙ ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን